# ከሰኔ 01/2014 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2014 ዓ.ም የነዳጅ ምርቶች

# የችርቻሮ መሸጫ ዋጋን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

የሚኒስትሮች ም/ቤት መስከረም 23 ቀን 2001 ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ የነዳጅ ምርቶች ዋጋ በየወሩ እንዲከለስ በሰጠው መመሪያ መሠረት ከሰኔ 01/2014 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2014 ድረስ ተግባራዊ የሚሆነው የነዳጅ ምርቶች የችርቻሮ መሸጫ ዋጋን አስመልክቶ ይህ መግለጫ ተዘጋጅቷል፡፡

የዓለም የነዳጅ ምርቶች የመሸጫ ዋጋ በየወሩ በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት የሀገራችን የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ በወቅታዊ የዓለም ነዳጅ ዋጋ መሠረት ተሰልቶ ተግባራዊ ቢደረግ አሁን በተግባር እንዲሸጥበት ከተወሰነው የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ የተለየ ይዘት ይኖረው ነበር፡፡

ነገር ግን መንግስት የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች በተረጋጋ ሁኔታ እንዲቀጥሉ ለማስቻል በሰኔ ወር/2014 ዓ.ም የቤንዚን፣ የናፍጣ እና የኬሮሲን (ነጭ ጋዝ) የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ በግንቦት ወር ሲሸጥበት በነበረው ያለምንም ለውጥ በነበረበት እንዲቀጥል ተወስኗል፡፡

ነገር ግን የአውሮፕላን ነዳጅ፣ ቀላል ጥቁር ናፍጣ እና ከባድ ጥቁር ናፍጣ የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ በዓለም አቀፍ ዋጋ ተሰልቶ የመጣው ልዩነት ሙሉ በሙሉ ወደ ተጠቃሚው እንዲተላለፍ የተወሰነ መሆኑን እያሳወቅን የነዳጅ ምርቶች ወቅታዊ የዓለም አቀፍ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ሸማቹ ህብረተሰብ ምርቶቹን በቁጠባ የመጠቀም ባህሉን በማዳበር እና ህገ ወጥ ንግድን በመከላከል መንግስት ለዘርፉ የሚያወጣውን ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ እንዲሁም ድጎማ ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የራሱን ኃላፊነት እንዲያበረክት ጥሪ እያቀረብን በዓለም ገበያ ላይ የሚኖረውን የነዳጅ ዋጋ መነሻ በማድረግ እንደ አስፈላጊነቱ ማስተካከያ ሊደረግ የሚችል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ግንቦት 22 ቀን 2014 ዓ.ም

የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

The Federal Democrataic Republic Of Ethiopia
Ministry Of Trade & Regional Integration

ግንቦት 2 2 2014
ቀን /Date —/—/—
ቁጥር/No 01-1-22-9/9939

Rectangular Snip

ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን
ለፋና ብሮድካስት ኮርፖሬሽን
ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት
ለዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል
ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፦ ከሰኔ 01/2014 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2014 የነዳጅ ምርቶች የችርቻሮ መሸጫ ዋጋን ይመለከታል፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት መስከረም 23 ቀን 2001 ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ የነዳጅ ምርቶች ዋጋ በየወሩ እንዲከለስ ውሳኔ ማሳለፉ ይታወቃል፡፡

በዚህም መሠረት ከሰኔ 01/2014 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2014 ዓ.ም የነዳጅ ምርቶች የመሸጫ ዋጋ በተመለከተ የተዘጋጀ መግለጫ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

እንዳለው መኮንን አሰሜ
ሚኒስትር ዴኤታ

አባሪ፦ 1 ገጽ

እንዲያውቁት
- ለክቡር የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር

  ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

ግልባጭ፦
- ለንግድ እና የንግድ ውጤቶች አቅርቦትና ስርጭት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን

  አዲስ አበባ
- ለህዝብ ግንኙነት እና ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት
- ለንግድ ዕቃዎች ዋጋ ጥናት፣ ክትትል እና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት

  ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር



SHOT ON SMART 4